EthioLion

# አበባ

እድሜ እለምን ነበር ለመቆየት
ወግ ማረግ ደስታን ላይበት
በአይምሮ በኑሮ ላድግበት
ወጥቼ ወርጄ ነበር አቀበት
ደግ ዘመን አያለሁ በማለት

እድሜው  አልቆ ቀኑ ቀርቦ
ደግ ዘመን ለማየት  በደቦ
ተመካክሮ ነበር ታስቦ
ደግ ዘመን መምጫው ቀርቦ

አየው ይሆን ቀረብኩኝ
ዘመኑ ሲመጥቅ ታይቶኝ
እደርስ ይሆን ጓጓሁኝ

ከዋክብት የምድሩ ፍጥረታት
ሰምቼ ነበር ብስራት
አበባ ፈንድታ ለማየት
ከንቱ መልፋት መዋተት
አበባን ለማየት መጓጓት

አበባን ሳናይ ዘመኑ ቀርቧል
አዲስ ዘመን አልመስልህ ብሏል
ሰው በሰው ላይ አምጿል
ከሚበላው የማይበላው ሞልቷል
አውሬው በከተማ ሰልጥኗል

ያለአበባ ዘመን ሲለወጥ
አገሩ ባዶ ሆኖ መደንገጥ
ሁሉም ከመሄድ ላያመልጥ
ነብሰ ገዳይን መለማመጥ

አልተለመደም ነበር በዚያ ዘመን
እየሞቱ አዲስ ዘመን
ማን እረግሟት ይሆን ምድሪቱን
ሰላም እንዳናይ ሽፈኑን

የደስታ የሰላም ምልክት
የምድር የቤቱ በረከት
ሰላም ሰፍኖ ማየት
ነበር የሁላችን ምኞት

የልፋት የድካም ውጥቱ
በቀኑ ተገኝቶ መለየቱ
የዘመኑ ማብቂያ ምልክቱ
አበባን ሳናያት መምሸቱ
አይቀርምና ያቺን ቀን ማየቱ

የአዳም ልጅ ሁሉ እዳው
እንዳበባዋ መክሰም ነው
ቢያውቀው ቀኑን ቢያሰላው
እስከወዲያኒው እጥው ፈንታው
እንዳበባዋ እርግፍ ነው

ወንድወሰን ሰብስቤ
Coventry

Ethiopia Will Prevail!